# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"…እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" ኢሳ 48፥17

God's Love, P.O.Box 6734, L.S. MO 64064
mtizazu@hotmail.com -----Fax 816 – 246 - 9395

**መጋቢት 1994 MARCH 2002**

**"ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል ።" ኢሳ 54 ፥ 13**

# እግዚአብሔርን መስማት

. በእግዚአብሔር መሰማት

ፀሎቴ ተመልሶ እንደሆነና እንዳልሆነ እንዴት አው ቃለሁ? ይህ በዘመናት ሁሉ የነበረ ጥያቄ ነው። የዕም ነት አባቶችም ጥያቄ ነበረ። ነፍሳችንን በእግዚአብሔር ፊት በፀሎት አፍስሰን ከቃተትን በኋላ የእግዚአብሔር መልስ ሁል ጊዜ ግልጽ ሆኖ አይታይም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ፀሎትን ሰምቶ የሚመልስ አምላክ ለመ ሆኑ ብዙ መረጃዎች አሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደም ንረዳው እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር የሚነጋገርበት መንገድና አኳኋን ውስን አይደለም። ከዚህ ቀጥሎ እግዚአብሔር የተናገረባቸውን ልዩ ል ዩ መንገዶችና ሁኔታዎች ከቃሉ እንመለከታለን።

የእግዚአብሔር ካሕን የነበረው ዘካሪያስና ባለቤቱ ኤ ልሳቤጥ ልጅ አልነበራቸውም። ኤልሳቤጥ መካን ነበረ ች። ስለዚህም ነገር ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአ ብሔር ይፀልዩ ነበር። የሉቃስ ወንጌል 1፥ 8 - 13 እንዲህ ይላል ፡-

"እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገ ለግል፥እንደ ካሕናት ሥርዓት ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት። በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር። የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው። ዘካሪያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ፥ፍርሐትም ወደቀበት። መልአኩም እንዲ ህ አለው፡- ዘካሪያስ ሆይ! ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አት ፍራ ፡ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ፡ ትወልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ።"

በሌላ ሁኔታ ስለ ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 18 ፥ 9 - 10 የተመለከተውን እናገኛለን። ሐዋሪያው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በትጋት በመስበኩ ምክንያት ማስፈራራትና ማሳደድ ይደርስበት ነበር ። በዚያን ጊዜ የጌታ መልስ የመጣው <u>በራዕይ</u> መልክ ነበር። እንዲህ ይላል " እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ፥ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፥ ነገር ግን ተናገር ፡ ዝምም አትበል ፤ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና አለው።"

በሌላ ሁኔታ ደግሞ እግዚአብሔር ከዚህ በተለየ መን ገድ ሲናገር እናገኛለን። የናቡከደነጾር ልጅ ብልጣሶር ከኢየሩሳሌም የተማረኩ ክቡርና ቅዱሳን ዕቃዎች በቤተመንግሥቱ ውስጥ ነበሩት። ከዕለታት አንድ ቀን በአንድ ድግስ ላይ በሰከረ ጊዜ የከበሩትን ዕቃዎች አስ ወጥቶ ተጠቀመባቸው። የእግዚአብሔርም ዕቃ ክብር ከመደፈሩ የተነሣ የቁጣው መልዕክት መጣ። "በዚያ ም ሰዓት <u>የሰው እጅ ጣቶች</u> ወጥተው በንጉሡ ቤት በ ተለሰነው ግምብ ላይ በመቅረዙ አንጻር ጻፉ፥ ንጉሡም የሚጽፉትን ጣቶች አየ። የዚያን ጊዜም የንጉሡ ፊት ተለወጠበት፥ አሳቡም አስቸገረው፥ የወገቡም ጅማቶች ተፈቱ፥ ጉልበቶቹም ተብረከረኩ።" ትንቢተ ዳንኤል 5 ፥ 5 - 6 "የተጻፈውም ጽሕፈት ማኔ፡ቴቄል፡ ፋሬስ ይላል ። (ትንቢተ ዳንኤል 5፥25)

በ<u>መልአክ፥በራዕይ፥ በአስገራሚ ጣት</u> የእግዚአብሔር መልእክት (መልስ) ሲመጣ አየን። ለሙሴ ግን በእሳት ነበረ። "የእግዚአብሔርም መልአክ <u>በእሳት ነበልባል</u> በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው ፤ እነሆም ቁጥቋጠው በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጠውም ሳይቃጠል አየ ። … እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ ሙ ሴ ሙሴ ፡ ሆይ፡ አለ…።" (ኦሪት ዘጸአት 3 ፥ 2 - 4)

በሕልም ሲናገር ፡- "(ያዕቆብ) <u>ሕልምም አለመ</u> ፤ እነሆም መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ፥ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ፥እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ይወ ጡበት ይወርዱበት ነበር። እነሆም እግዚአብሔር በላ ይ ቆሞበት ነበር፥እንዲህም አለ…" (ኦሪት ዘፍጥረት 28፥12) "<u>ዮሴፍም ሕልምን አለመ</u> ለወንድሞቹም ነገራቸው፤ … ።" ( ዘፍጥረት 37 ፥ 5 )

የቅድስት ማሪያም እጮኛ ዮሴፍ በድንግሊቱ ጸን ሳ መገኘት በተቸገረ ጊዜ ሕልም አየ። "እነሆ የጌታ መልአክ <u>በሕልም ታየው</u>፥እንዲህም አለ፡-- የዳዊት ል ጅ ዮሴፍ ሆይ ፥ ከእርሷ የተጸነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ ። ል ጅም ትወልዳለች፤እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድ ናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።" (ማቴዎስ 1፥ 20-21)

የዚህ መልእክት ዋና ዓላማ የእግዚአብሔር ድምፅ በብዙ አኳኋን ሊመጣ እንደሚችል ማሳሰብ ነው። ለዚህም የሚከተለው የመጽሐፍ ክፍል መሪህ ምሳሌ ይሆነናል፤ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ባይጻፍ ኖሮ ክርስቲ ያኖችም ሳንቀር ለማመን በተቸገርን ነበር። የበለዓም ታሪክ ነው። እርሱም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በሆነ ሁኔታ በአህያው ተቀምጦ ይጓዝ ነበር። "አህያይ ቱም የእግዚአብሔርን መልአክ አየች ከበለዓምም በታ ች ተኛች፥ በለዓምም እጅግ ተቆጣ፥አህያዪቱንም በበ ትሩ ደበደባት። እግዚአብሔርም <u>የአህያዪቱን አፍ ከፈተ</u>፥በለዓምንም ሦስት ጊዜ የመታኸኝ ምን አድርጌ ብህ ነው? አለችው። … እግዚአብሔርም የበለዓምን

ዓይኖች ከፊተ የእግዚአብሔርን መልዓክ በመንገድ ላይ ቆሞ ፡ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ ... ::" ( ዘኍልቁ 22 ÷ 27 ÷ 31 )

ዛሬ አህዮች የማይናገሩ ይመስላል:: አህያችንም ወዳ አሰኘን አቅጠጫ አልነዳ ሲል ዱላ ለማንሣት እንቃጣለን:: ነገር ግን እግዚአብሔር የበለዓምን ዓይኖች እስከ ከፊተ ድረስ በለዓም ከአህያው ጋር እንደ ሰው ቆሞ ሲከራከር እንኳ አይደነቅም ነበር:: *ባለቤቱን የሚደበድብ÷ልጆቹን የሚደበድብ÷ጓደኞቹን የሚደበድብ÷ቤተክርስቲያንና በመሥሪያቤት የሚደባደብ ገና ዓይኖቹ ያልተከፈቱለት የዘመኑ በለዓም ስንት አለ ? እግዚአብሔር ዓይኖቻችንን ይክፈትልን::*

ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎች አምላካችን እግዚአብሔር ፀሎትን ሰምቶ ለመመለስ በብዙ አኳኋኖች ሊመጣ እንደሚችል አይተናል:: ከተገለጸው ቃሉ ጀምሮ ወሰን በሌላቸው መንገዶች ሲናገረን ሰምተን በዕምነት ካልተቀበልነው ቃሉ ሳይጠቅመን ይቀራል:: "*ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ÷ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን*፤... (ዕብራውያን 1÷1-2)

ኢየሱስ ሲናገር ዛሬ የምንሰማው ስንቶቻችን እንሆን? ኢየሱስን መስማት ለመማር የምንተጋስ ስንቶች ነን? በቅርቡ ድምፁን ሰምተን እናውቃለን? ወይስ ድምፁን አለመስማታችን ይገደናል? ጌታን መስማት ለአንዳንድ ዕድለኞች እንጂ ለእኔ አይደለም ብለን ትተናል? ጨዋና ዝግተኛው ድምፁ ኢየሱስን አምኖ ለተቀበለው ልባችን ሲሰማ እንታዘዝ:: ለተጻፈው ቃሉ እንታዘዝ:: እግዚአብሔርን ለመስማት ታላላቅ ድንቆችና ተዓምራት አያስፈልጉም:: ከመታዘዝ በኋላ ነው የጠለቀውን የጌታን ነገር ወደ መስማት የምናድገው:: አህያችን አልሄድ ሲል ዱላ ከመምዘዝ ይልቅ (ሊያነጋግረን በዙሪያችን የቆመውን የጌታ መልዓክ) ዞር ዞር ብሎ በፀሎት መፈለግ ማስተዋል ነው:: መላኩም ተው÷ተመለስ ቢል ፈጥኖ መመለስ አስተዋይነት ነው፡ "ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፡- ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት÷ አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት የመረመሩበትም አርባ ዓመታትም ሥራዬን ያዩበት በምድረ በዳ በፈተና ቀን በማስመረር እንደ ሆነ÷ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ::" (ዕብራውያን 1÷7-9) ሰው በየዕለቱ እግዚአብሔርን መስማት እንዲችል በመጀመሪያ በጌታ በኢየሱስ ያለውን የንስሐ ሕይወት መጠበቅ አለበት፤ከዚያም ሁልጊዜ ጆሮችን አቅንቶ መጠባበቅ ያሻል:: የፀሎት መልስ ልዩ ምሪት÷ወይም ልዩ መረዳት ከእግዚአብሔር መስማት የሚወድ፡- ድምፁ በሚገኝባቸው ሥፍራዎች ፡- በቃሉ ንባብ÷በወንጌል ስብከት÷እግዚአብሔር በዕውነትና በመንፈስ ቅዱስ በሚመለክበት ሥፍራ ሁሉ ÷ ሆን ብሎ በማስተዋል ማዳመጥ ያስፈልገዋል:: የጌታ ድምጽ ለሚወዱትና ተግተው ለሚፈልጉት ሊገኝ ዝግጁ ነውና:: እግዚአብሔር ይመስገን::

## ኢየሱስ ጌታ ነው
## ጌታ ይባርክህ

# ፍቅር ደጅ አደረ

የተጠናወተን ጨለማው ጠጠረ
በዋዛ አይጨበጥ ብርሃንም ከበረ
አበው ያስተማሩን ደግነት ተሻረ
የጌታም ምሕረቱ በእኛ አልተከበረ
ይኸው በእኛም ዘመን ፍቅር ደጅ አደረ::

ፍቅር ቀዘቀዘ ÷ መዋደድ ተሳነን
ጦርነት ሳናውጅ ሰበብም ሳይኖረን
የጉድ የሰው ነቀዝ ውስጥ ውስጡን ተባልተን
ባዛኝ አሳዛኞች ፍቅር ያልሆነልን
ብኩን ዕምነት አልቦ መንፈስ የጐደለን
ለብ ለብ በፍቅር እንዲሁም ግብራችን
አለን ባገራችን ፍቅርን እደጅ ትተን::

ተግተን እንዳንሠራ ከበደን ድካሙ
በብዙም ስንፍና ያሰጋናል ጾሙ
ድንቁርና ክፉ የጨለማ ሥራ
ከዕውቀትም ጋራ ብዙ አለ መከራ
ቀኙንም ከዳነው ግራም አልሠራልን
በዚያኛው አመፅን ይኸኛው አፋጀን
የሕይወት መልካችን በቁም የከሰረ
በእኛስ ባገራችን ፍቅር ደጅ አደረ::

ሞኝነት አልመረጥን እንዳይናጠቁን
ብልጠትም አይሠራም ያሳዝናል ጌታን
ማሸነፍ መሰለን ሌሎች የሚጐዳ
መዋጥም መሪር ነው የሽንፈትን ፍዳ
የብርሃን የጨለማ የሁለቱም ባለ ዕዳ
በዚህ ሁሉ መኸል ፍቅራችን ተጎዳ::
በሞትና በሕይወት በሁለቱም ተከሳሽ
በጥበብ በስንፍና በጋራ ተወቃሽ
ወዳጅን የጠላ ጠላትን ያልማገረ
በፍቅር በጥላቻ በአንዱም ያላማገረ
እኛስ ባገራችን ፍቅር ደጅ አደረ::

ፈርሐ እግዚአብሔር መክሰር የመሰለን
ንፉግና ግብዝ አፋዊ ትጉሃን
ትንሣኤ ብንወድም መስቀልን አንሻም
መልቀቅ ይሳነናል መያዝም አንችልም
በሕይወት ላይ መሞት እየተማገረ
በእኛስ ባገራችን ፍቅር ደጅ አደረ::

ሁሉ ባገር ሞልቶ ፍቅር የጎደለን
ጣዕመ ዜማ አልቦ ከንቱ ጸናጽል ነን
እንኳ በሰው ቋንቋ የመላክት መናገር
ለነገድ ለጐሳ ሳይበጅ ያለ ፍቅር
ጋብዙት ግባ በሉት በእኛ መኸል ይደር
በእኛም ባገራችን ፍቅር ገብቶ ይኑር::

እኛ ነን ተረኞች የፍቅር ባለሳምንት
ፈጥነን እጆቻችንን ወደ ላይ በማንሣት
ሁሉንም ለገዛው ራስን በማስገዛት
እኛም ባገራችን ፍቅር ይደርባት::
እግዚአብሔር ለሰዎች በፍቅሩ የሰጠው
በቶሎ መጋበዝ ፍቅርስ ኢየሱስ ነው::

መላኩ ትዕዛዙ